# አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

**ከፍተኛ  የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የራሳቸውን አማራጭ የውሃ መገኛዎችን አጎልብተው እንዲጠቀሙ የሚያስችል መምሪያ ቁጥር 8/2012**

## መግቢያ

ባለስልጣኑ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሚያቀርበውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ በጥራትና በመጠን በማሳደግ ስርጭቱን ለማስፋት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ የሚገኝ ሲሆን በከተማው መስፋት እና የህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የዉሃ ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ያለዉን ዉስን የዉሃ ምርት ለከተማዉ ነዋሪ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለማከፋፈል በማስፈለጉ፡፡

በጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት በተቋቋመው ዴሊቨሪ ዩኒት በከተማዉ ዉስጥ የሚስተዋለዉን የውሃ እጥረት ችግር ለመፍታት ባለስልጣኑ ለከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚዎች የሚቀርበዉን የውሃ መጠን በመቀነስ ወደ ህዝቡ የሚሰራጨዉን የዉሃ መጠን እንዲጨምር ማድረግ ያለበት መሆኑ በመታመኑ ፡፡

ባለስልጣኑ ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የሚያቀርበዉን ንጹህ ዉሃ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለማሰራጨት እንዲችል ለከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚዎች የሚያቀርበዉን የውሃ መጠን በመቀነስ ወደ ህዝቡ የሚሰራጨዉን የዉሃ መጠን ለመጨመር ይረዳው ዘንድ ከፍተኛ የዉሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የራሳቸዉን አማራጭ የዉሃ መገኛ እንዲያጎለብቱ እና እንዲጠቀሙ ማድረጉ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑ ስለታመነ ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀፅ አንድ
### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የራሳቸውን አማራጭ የውሃ መገኛዎች አጎልብተው እንዲጠቀሙ የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 8/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## <u>አንቀፅ ሁለት</u>
## <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ

1. **"ባለሥልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችንም ያጠቃልላል፡፡
2. **"ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኛ"** ማለት ከቆጣሪ ብልሽት ውጪ ዜሮ ንባብ ሳያስመዘግብ የ12 ወር ንባብ ተወስዶ በአማካይ በወር 500 ሜትር ኪዩብ ውሃ የሚጠቀም ደንበኛ ነው፡፡
3. **"አማራጭ የዉሃ መገኛ"** ማለት ባለስልጣኑ ከሚያቀርበዉ ንጹህ ውሃ ዉጪ ሌላ ማንኛዉም የዉሃ መገኛ ሲሆን የጉድጉድ ዉሃ፣ የዝናብ ዉሃ ፣ የወንዝ ዉሃ ፣ የከርሰምድር ውሃ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ፡፡

## <u>አንቀፅ ሶስት</u>

## <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚ የውሃ ደንበኞች፣ ተቋማት እና ወይም በከተማ ውስጥ የሚገኙ ከመጠጥ ውሃ ውጭ ለሆኑ አገልግሎቶች አማራጭ የውሃ ምንጭ በሚፈልጉ እንዲሁም አማራጭ የውሃ ምንጭ በማጎልበት በመጠቀም ላይ ባሉ ግለሰቦች፣ ተቋማት እንዲሁም ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>ተግባር፣ ኃላፊነትና ግዴታዎች</u>
## <u>አንቀፅ አራት</u>

## <u>የከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኛ ግዴታዎች</u>

1. ከባለስልጣኑ የሚሰጠዉን ንጹህ ዉሃ በቁጠባ በመጠቀም፤ ከመጠጥና ከምግብ ማዘጋጃነት ዉጪ ለሌላ አገልግሎት ያለመጠቀም ሃላፊነት አለበት፤
2. የራሱን የዉሃ መገኛ ምንጭ የማጥናት ፣ የማጎልበት እና እንደ ሁኔታዉ ለተለያዩ አገልግሎቶች የመጠቀም ግዴታ አለበት፤
3. ባለስልጣኑ ደንበኛዉ ያጎለበተዉን አማራጭ የዉሃ መገኛ ምንጭ ለመጎብኘት በፈለገ ጊዜ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለበት፤

4. በተለያዩ ቴክኒካል ምክንያቶች አማራጭ የውሃ ምንጭ መገኛው ችግር ሲያጋጥመው ወይም ሲቆም በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩን መፍታት ይኖርበታል፡፡
5. ያጎለበተውን አማራጭ የውሃ ምንጭ የውሃ መጠን መሰረት በማድረግ  የተለያዩ መንገዶችና አማራጮችን በመጠቀም ባለስልጣኑ የደንበኛውን የቀድሞ የውሃ አቅርቦት ለመቀነስ  ለሚያደርገው አሰራር ተባባሪ የመሆን ግዴታ አለበት፤
6. ያጎለበተውን አማራጭ የውሃ ምንጭ የውሃ መስመር ባለስልጣኑ ከሚያቀርበው የውሃ መስመር ጋር  ማገናኘት  ወይም ማያያዝ የለበትም ፡፡
7. አማራጭ የውሃ ምንጭ ሲያጎለብት ወይም እንደያጎለብት ትእዛዝ ተሰጥቶት ተግባራዊ ሲደረግ ስለአማራጭ የውሃ ምንጩ ዝርዝር መረጃ  ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
8. ያጎለበተው አማራጭ ውሃ በተለያየ ቴክኒካል ችግር አማካኝነተ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም ባለስልጣኑ ከሚያጎለብተው  ወይም ከሚያቀርበው የውሃ መገኛ ቦታ ገዝቶ ከመጠቀም ውጪ ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ ወደ ቀድሞው የውሃ አጠቃቀም የመመለስ እና የአቅርቦት ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ ህገ-ወጥ አጠቃቀምን ማከናወን አይችልም፡፡
9. ደንበኛው ባለስልጣኑ ከሚያጎለብተው ወይም ከሚያቀርበው አማራጭ የውሃ ምንጭ መገኛ ቦታ መጠቀም የሚችለው ባለስልጣኑ የሚያስቀምጠውን የአሰራር ስርዓት ጠብቆ መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ አምስት

## የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. በአካባቢዉ ስለሚገኘዉ አማራጭ የዉሃ መገኛ መረጃ እና የምክር አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤
2. ደንበኛዉ ሲፈልግና ሲጠይቅ ስለ ውሃ አጠቃቀምና ማጣራት ሂደት የማማከር አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤
3. ደንበኛዉ የዉሃ ጥራት ቁጥጥር ለማድረግ ሲፈልግና ሲጠይቅ የላብራቶሪ አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤
4. ደንበኛዉ ያጎለበተዉ የውሃ ምንጭ ችግር ሲገጥመዉ የጥገና ባለሙያ በመመደብ የጥገና አገልግሎት ድጋፍ የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤
5. በመመሪያው አስፈላጊነት እና አፈፃፀም ዙሪያ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ መመሪያው እንዲከበር የማድረግ ሃላፊነት አለበት፤
6. በመመሪያው ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት በተቋሙ የህዝብ ክንፍ በኩል ከከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች ጋር መወያት እና መግባባት ላይ የመድረስ ሃላፊነት አለበት፤

7. አማራጭ የውሃ ምንጭ እንዲያጎለብቱ ትዕዛዝ የተሰጣቸውን ወይም አጎልብተው በመጠቀም ላይ ያሉ ከፍተኛ ተጠቃሚዎችን የአጠቃቀም ሁኔታ የመከታተል የመቆጣጠር እንዲሁም የመደገፍ ሃላፊነት አለበት ፡፡
8. ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚዎች አማራጭ የውሃ ምንጭ አጎልብተው መጠቀም ሲጀምሩ የቀድሞውን የውሃ አቅርቦት በመቀነስ የአካባቢው የውሃ ስርጭት በሚሻሻልበት ሁኔታ ላይ ጥናት በማድረግ ተግባራዊ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፤
9. ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚዎች አማራጭ የውሃ ምንጭ በተለያየ ችግር ምክንያት አገልግሎት መስጠት ሲያቆም በማጣራት ባለስልጣኑ ከገነባው ወይም ከሚያቀርበው አማራጭ የውሃ ምንጭ መገኛ ደንበኛው እንዲጠቀም የማመቻቸት ሃላፊነት አለበት፡፡
10. ማንኛውም ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ የጉድጓድ ወይም ማንኛውንም አማራጭ ውሃ የማጎልበት ስራ ከመጀመሩ በፊት ከባለስልጣኑ ፈቃድ እንዲያገኝ ያደርጋል፣ ስራው ተጀምሮ ከሆነም ደንበኛው ፍቃድ የተሰጠው መሆን አለመሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡
11. አማራጭ የውሃ ምንጭ በማጎልበት እና በመገንባት ሒደት የሚፈጠሩ አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን በተመለከተ ተገቢውን ጥናት ያደርጋል፡፡
12. ባለስልጣኑ ለአማራጭ የውሃ ምንጭነት የሚያጎለብቱ የውሃ ምንጮችን የውሃ ጥራት ደረጃ እንዲሁም ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ለተጠቃሚው ወይም ለአማራጭ የውሃ ምንጭ አጎልባቹ የማሳወቅ ሃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀፅ ስድስት</u>

## <u>የባለስልጣኑ መብት</u>

1. አማራጭ የውሃ አቅርቦት ከማጎልበት የግንባታ ስራ ጀምሮ ለስርጭት ወይም ለማጓጓዝ የሚወጣውን ወጪ መነሻ ያደረገ የታሪፍ ማሻሻያ /ክለሳ/ የማድረግ መብት አለው፡፡
2. ከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚዎች በማጎልበት እየተጠቀሙበት የሚገኝን አማራጭ የውሃ መገኛ ለህዝብ ጥቅም መዋል የሚገባው መሆኑ በጥናት ሲረጋገጥ ደንበኛው ወይም ድርጅቱ ለግንባታ ያወጣውን ወጭ ክፍሎ በመውረስ ለህዝብ አገልግሎት የማዋል መብት አለው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ ሰባት

### ተጠያቂነት

1. በዚህ መመሪያ የውስጥ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና የሐሰት ማስረጃ ያቀረበ እንዲሁም የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ያደናቀፈ ደንበኛ አግባብ ባላቸው የባለስልጣኑ መመሪያዎችና የሃገሪቱ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡
2. የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ያደናቀፈ ወይም ትርጉሙን እና አሰራሩን ያዛባ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የባለስልጣኑ የስራ ኃላፊና ሰራተኛ በፍ/ብሔርና የወንጀል ህግ ያለው ተጠያቂነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ በህብረት ስምምነቱ እና በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተገቢው የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

### አንቀፅ ስምንት

### ክልከላ

1. ማንኛውም ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ያጎለበተው አማራጭ ውሃ በተለያየ ቴክኒካል ችግር አገልግሎት መሰጠት ሲያቆም ከባለስልጣኑ እውቅና ውጪ ወደ ቀድሞው የውሃ አጠቃቀም በመመለስ ባለስልጣኑ ከሚያሰራጨው ውሃ መጠቀም የተከለከለ ነው ይህን ክልከላ በመተላለፍ ድርጊቱን ፈፅሞ የተገኘ መንኛውም ደንበኛ ባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎቱን የማቋረጥ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገሪቱ ህግ መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል ፡፡
2. ማንኛውም ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚም ሆነ ማናቸውም ሰው በቅድሚያ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ አማራጭ የውሃ መገኛ የማጎልበት ስራ መጀመርም ሆነ አጎልብቶ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ይህን ክልከላ በመተላለፍ ድርጊቱን ፈፅሞ የተገኘ መንኛውም ደንበኛም ሆነ ማንኛውም ሰው በሀገሪቱ ህግ መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

### አንቀፅ ዘጠኝ

### መመሪያውን የማሳወቅ ግዴታ

ማንኛውም የባለስልጣኑ ሃላፊ ፣የሥራ ክፍል እና ሰራተኛ የሚመለከታቸውን አካላት እና የባለስልጣኑ ደንበኞች ስለመመሪያው አፈፃፀም በቂ እውቀት እንዲኖራቸው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ አስር

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀፅ አስራ አንድ

## የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የባለስልጣኑ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች የሚመለከታቸው አካላት እና ደንበኞች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ አስራ ሁለት

## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀፅ አስራ ሶስት

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞና የባለሥልጣኑ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አወቀ ኃይለማርያም
የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን
ዋና ሥራ አስኪያጅ